የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

Central Ethiopia Regional State

Investment & Industry Development Bureau

ቁጥር ዐ/ግ/ጉ/ኢ/ፋ/ዐ2/12/02
Ref.No

ቀን 6/11/2018
Date

ለ..........ዞን ኢንቨ/ኢንዱ/ ልማት መምሪያ

ለ..........ል/ዩ ወረዳ ኢንቨ/ኢንዱ ልማት ጽ/ቤት

ባሉበት፤

ጉዳዩ፡ የአሰራር መመሪያ ስለመላክ ይሆናል፡፡

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥ የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በክልሉ አስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ (ሀ) በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ፣ አሠራሮችን ግልጽና ወጥ ለማድረግ እንዲሁም ቀልጣፋ የሕዝብ አገልግሎት አሰጣጥን ለማስፈን የተለያዩ የሕግና የአሠራር ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና በማስተግበር ላይ ይገኛል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በክልላችን ኢንቨስት ለማድረግ ጥያቄ የሚያቀርቡ ባለሀብቶች በፕሮጀክት ፕሮፖዛላቸው ላይ በቅድመ ሁኔታነት ሊያሟሏቸው የሚገቡ፣ በተለይም ፕሮጀክቱን በተግባር ላይ ለማዋል የሚያስፈልገውን የካፒታል መጠን እና የመሬት ፍላጎትን ፍትሐዊና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመወሰን የሚያስችል "የአሠራር መስፈርት (Standard)" ተዘጋጅቷል፡፡

ይህ የአሠራር መስፈርት (Standard) ባለሀብቶች የሚያቀርቡት የካፒታል መጠንና የሚጠይቁት የመሬት ስፋት ከተግባራዊ የኢኮኖሚና የልማት እውነታዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ለመመዘንና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ወጥ መመሪያ ነው፡፡

ስለሆነም የተዘጋጀውን ዝርዝር የአሠራር መመሪያ ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር .... ገጽ አያይዘን የላክን መሆኑን እየገለጽን፣ መመሪያው በክልሉ ፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ ከጸደቀበት ቀን 30/10/2018 ዓ.ም ጀምሮ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ማስተናገድ የሚቻለው በጸደቀው መመሪያ መሰረት ብቻ እንዲሆን እናሳስባለን፡፡

ከሰላምታ ጋር!

ዶ/ር አባስ መሐመድ አህመድ
የኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ
ልማት ቢሮ ኃላፊ
Dr. Abas Mohammed Ahmed
Investment & Industry
Development Bureau Head

ግልባጭ፡-

- ለቢሮ ኃላፊ
- ለኢንቨ/ዲያስፖራ ዘርፍ ሀላፊ
- ለኢንዱስትሪ ዘርፍ ሀላፊ

ቡታጅራ፤

Tell:-0461451864/0461451649/0461457566 email:-cerinvestindustry@gmail.com
Website:-https://www.cerlidb.gov.et https://www.facebook.com

ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

<u>ቡታጅራ</u>

ጉዳዩ: <u>የመመሪያ ምዝገባ ማሳወቅን ይመለከታል።</u>

በቀን 26/10/2018 በቁጥር ማ/ኢ/ኢ/01/2395/06 ከቢሯችሁ በተጻፈ ደብዳቤ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የቢሮውን ተልዕኮ ለማሳካትና የሚያስችሉ እና ሥራዎችን በህግ መሠረት ለመሥራት የሚያግዙ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎች ማለትም በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የወጡ፦

1. በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ የኢንቨስትመንት መሬት በምደባ የሚተላለፍላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት እና የካፒታል መጠን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ፣
2. የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ እንዲመዘገብልን በማለት መጠየቃችሁ ይታወሳል።

በዚህ መሰረት ከተቋማችሁ የመጡትን መመሪያዎች በጥልቀት ፈትሸን አስፈላጊውን የመመሪያ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት የተከተሉ መሆናቸውን ያረጋገጥን ሲሆን በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀፅ 16/2 መሰረት በዛሬው ቀን ማለትም ሰኔ 30 ቀን /2018 ዓ.ም፣

1. የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ የኢንቨስትመንት መሬት በምደባ የሚተላለፍላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት እና የካፒታል መጠን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ፣ **መመሪያ ቁጥር 91/2018፣**

P.O.Box /ፖ.ሳ.ቁ/ TEL./ስልክ ቁጥር 0465562139 ሀላባ- ኢትዮጵያ
ዌብሳይት፦ www.cerjustice.gov.et, email: cerjustice@gmail.com. ቴሌግራም፦ t.me/cerjustice

2. የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ መመሪያ **መመሪያ ቁጥር 92/2018፤**

ሆና የተመዘገቡ መሆናቸውን እየገለፅን በክልሉ አስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 23/2016 አንቀፅ 17/2/ መሠረት ተቋማችሁ መመሪያዎቹን ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል ለተጠቃሚዎች በመመሪያው ይዘት ላይ ሰፊ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እንዲሰራ፣ መመሪያዎችን ስካን በማድረግ በፒ.ዲ. ኤፍ (PDF) ፎርማት በቢሯችሁ ድረ-ገጽ ላይ እንዲጫን እንዲሁም መመሪያዎችን በማሳተም ለሚመለከታቸው መንግስታዊና ሌሎች ባለድርሻ አካላት እንዲሰራጩ ወይም ማንኛውም የመመሪያዎቹን ቅጂ ማግኘት ለሚፈልግ ሰው መመሪያዎቹ ባለበት ሁኔታ የመመልከት ወይም ወጪውን ችሎ ከቢሮአችሁ እንዲያገኝ እንዲደረግ እያሳሰብን የሁለቱ (02) መመሪያዎች በድምሩ 63 ገጾች የያዘውን ሁለት ጥራዝ ተመዝግበው ቁጥር የተሰጣቸውን መመሪያዎች በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት የላክን መሆናችንን እንገልጻለን።

ግልባጭ፡

- ለቢሮ ኃላፊ ፅህፈት ቤት ከሠላምታ ጋር
- ለህግ ጉዳዮች ዘርፍ
- ለህግ ጥ/ማ/ማ/ዳይሬክቶሬት
  ፍትህ ቢሮ

Abraham Birhu Abiza
ቢሮ ኃላፊ እና የህግ ጉዳዮች
ዘርፍ ኃላፊ
Head of Justice Bureau &

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ

"በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ የኢንቨስትመንት መሬት በምደባ የሚተላለፍላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት እና የካፒታል መጠን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2018"

ሰኔ 2018 ዓ.ም

ቡታጅራ፤

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት

ማዕከላዊ ነጋሪት ጋዜጣ

ቡታጅራ 3ኛ ዓመት ቁጥር
ሰኔ 2018 ዓ.ም

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Butajira 3rd Year No JULY /2026

"በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ የኢንቨስትመንት መሬት በምደባ የሚተላለፍላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት እና የካፒታል መጠን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2018"

መግቢያ

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ሀገር በቀልና አለም አቀፍ ባለሃብቶች፣ ድርጅቶች በክልሉ ያለውን ሰፊ የመልማት አቅም በመጠቀም የክልሉን ህዝብ የሚጠቅሙ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ይዘው እንዲመጡና በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲሳተፉ እየተከናወነ ያለውን ስራ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

አልሚ ግለሰቦች፣ማህበር እና ድርጅቶች ወደ ክልሉ በሚመጡበት ወቅት ያላቸውን ልምድ፣ አቅምና ተነሳሽነት ለመለየት እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ ተገምግመው መሬት በምደባ ለማስተላለፍ በሚኖረው ሂደት ውስጥ ወጥ የሆነ በመሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በአግባቡ የሚያሳይ አሰራርና መገምገሚያ መስፈርት በማስፈለጉ፤

ወቅታዊ አለማቀፋዊ፣ ሀገራዊ እና ክልላዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ መገምገሚያ መስፈርት/ ስታንዳርድ አዘጋጅቶ የተሻለ ልምድና የካፒታል አቅም ያላቸውን እንዲሁም ለስራ ዕድል ፈጠራ

እና ለቴክኖሎጂ ሽግግር የላቀ አስተዋጽኦ የሚኖራቸውን ባለሀብቶች /አልሚዎችን/ መልምሎ በክልሉ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲሰማሩ ለማስቻል በማስፈለጉ፣

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በምልመላ፣ መረጣና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት የሚስተዋሉ የቅልጥፍና እና የግልፀኝነት ክፍተቶችን በመቅረፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ አግኝተው ወደ ስራ የሚገቡበትን ሁኔታ ለመፍጠር የአሰራር ስርዓት ማስቀመጡ ተገቢ በመሆኑ፤

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል መንግሥት ኢንቨስትመንት እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በክልሉ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 199/2015 አንቀጽ 24(3) እና 39(2) በተሰጠው ስልጣንና ተግባር መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በክልሉ ምክር ቤት ውሳኔ የኢንቨስትመንት መሬት በምደባ የሚተላለፍላቸው የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት እና የካፒታል መጠን ለመወሰን የወጣ የአሰራር መመሪያ ቁጥር 91/2018" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1) "ክልል" ማለት የማዕካለዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ነው፡፡
2) "ቢሮ" ማለት የክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ነው፡፡
3) "ኢንቨስትመንት" ማለት አዲስ ድርጅት ለማቋቋም ወይም ነባር ድርጅት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ለመግዛት፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል በባለሀብት[1] በገንዘብ ወይም በዓይነት ወይም በሁለቱም የሚደረግ የካፒታል ወጪ ነው፡፡
4) "አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ" ማለት በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚሰማራ ባለሀብት የተጠየቀውን የካፒታል መጠን ፍሰት በማሟላት እንዲያለማና መብቱን

ተጠቅሞ ስራውን እንዲያከናውን ለማስቻል ስልጣን በተሰጠው አካል የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

5) "ድርጅት" ማለት ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ነው፡፡

6) "ካፒታል" ማለት የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ሀገር ገንዘብ፣ የሚተላለፍ ሰነድ፣ የማምረቻ ወይም የአገልግሎት መስጫ መሳሪያ፣ ህንፃ፣ የሥራ ማስኬጃ ካፒታል፣ የንብረት መብት፣ የአዕምሯዊ ንብረት መብት ወይም ሌላ የሚዳሰስ ወይም የማይዳሰስ ሀብት ነው፡፡

7) "30% የባንክ መረጃ" ማለት ባለሃብቱ ለፕሮጀክቱ ተግባራዊነት ካስመዘገበው ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ካፒታል/ብር ውስጥ መረጃውን ካቀረበበት ባንክ 30% አቅም ማሳያ የብር መጠን (clothing balance) የቅርብ ጊዜ የ6 ወር ገቢና ወጪ እንቅስቃሴ ያጠቃለለ ሆኖ የመጨረሻው ተንባቢ/ቀሪ ብር መጠን ማለት ነው፡፡

8) "መስፈርት/ ስታንዳርድ" ማለት በማንኛውም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ያሉ ፕሮጀክቶች የመሬትና የካፒታል መጠንን ለመወሰን የተዘጋጀ መመዘኛ መስፈርት ነው፡፡

9) "አግባብነት ያለዉ የኢንቨስትመንት መስሪያ ቤት" ማለት በክልል እና በዞን/በልዩ ወረዳ የኢንቨስትመንት መሬት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት እንዲሰጥ ቅድመ ሁኔታዎችን የሚያመቻች እና ኢንቨስትመንትን ለማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠዉ የየእርከኑ መስተዳድር አካል ነዉ፡፡

10) "የግብርና ኢንቨስትመንት ዘርፍ" ማለት በዓመታዊ ሰብሎች ልማት፣ የመካከለኛና ረዥም ጊዜ ቋሚ ተክሎች ልማት፣ የእንስሳት እርባታና ማድለብ፣ የተፈጥሮና ደን ልማት ሥራዎችን እና ሌሎች የግብርና ዘርፍ ስራዎችን አቀናጅቶ የያዘ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ነው፡፡

11) "የረዥምና የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች" ማለት ምርት ለመስጠት ከአንድ ዓመት በላይ ጊዜ የሚወስድባቸውና ምርት መስጠት ከጀመሩ በኋላ በተከታታይ ምርት የመስጠት ባህሪይ ያላቸው ሲሆኑ በዚህ መመሪያ ቋሚ ተክሎች ተብለው የተወሰዱትም እንደ ሙዝ፣ ቡና፣ ሻይ ቅጠል፣ ቃጫ፣ ፍራፍሬ ተክሎች፣ ጎማ ዛፍ፣ ሸንኮራ አገዳ እና የደን ዛፎች ልማት እና የመሳሰሉትንና ሌሎችን ያካትታል፡፡

12) "ዓመታዊ ሰብሎች" ማለት ምርት ለመስጠት ከአንድ ዓመት ያነሰ ጊዜ የሚወስድባቸው ሰብሎች ማለት ሲሆን እነሱም የአገዳና የብርዕ ሰብሎች (በቆሎ፣ጤፍ፣ ገብስ፣

እንደ፣ሩዝ)፣ የቅባት እህሎች እና ጥራጥሬ እንደ ሰሊጥ ፣ተልባ ፣ ማሽ ፣አተር ፣ ባቄላ ፣ሽንብራ ፣ምስር ፣ ቦሎቄ ፣ እና ሌሎችን ያካትታል፡፡

13) "የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ" ማለት በገጠርና በከተማ እሴት በመጨመር (value addition) ማምረት፣ ማኑፋክቸሪንግ፣ አግሮ ፕሮሰሲንግ፣ ጨርቃጨርቅ እና አልባሳት ማምረት፣ በማዕድን ላይ እሴት መጨመር፣ የተለያዩ ተሽከርካሪዎችን መገጣጠም፣ የተሽከርካሪ አካል ማምረት፣ ሌሎች መሰል ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች አቀናጅቶ የያዘ ዘርፍ ሲሆን በውስጡም የኢንዱስትሪ ፖርኮችንም አካቶ የሚይዝ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ነው፡፡

14) "የአገልግሎት ዘርፍ" ማለት በተለያዩ ባለኮከብ ደረጃ ሆቴል፣ ሎጅ፣ ሪዞርት፣ ሪል ስቴት፣ ሞቴል፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በማዕድን፣ በኮንስትራክሽን እና ሌሎች የአገልግሎት ዘርፎችን አካቶ የሚይዝ የኢንቨስትመንት ዘርፍ ነው፡፡

15) "መሬት" ማለት የተለያዩ የኢንቨስትመንት ተግባራትን ለማከናወን እንዲውል በየደረጃው ባሉ አስፈጻሚ አካላት የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ በምደባ እንዲተላለፍ ተደርጐ ለኢንቨስትመንት ጥቅም ላይ የሚውል የተፈጥሮ ሀብት ነው፡፡

16) "የሥራ ዕድል መፈጠር" ማለት ማንኛውም ወደ ሥራ የሚገባ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች በተቀመጠው መስፈርት/ ስታንዳርድ መሠረት ለዜጐች የሥራ ዕድል በመፍጠር ተጠቃሚ ማድረግ ነው፡፡

3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ያጠቃልላል፡፡

4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ በአሰራር የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መርምሮ የተሟላ ሆኖ ሲቀርብ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የመሬት እና የካፒታል መጠን ለማስተናገድ ሥልጣን በተሰጠው በቢሮው፣ በሁሉም የዞን ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያዎች እና በልዩ ወረዳ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የኢንቨስመንት ጥያቄ በሚያቀርቡ ባለሀብቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. ዓላማ

በቂ አቅምና የተሻለ ልምድ ያላቸው ባለሀብቶችን በመምረጥ በክልሉ በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲሰማሩ በማስቻል ውስን የሆነውን የመሬት ሀብት ግልፅ፣ ወጥ፣ ፍትሀዊና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለፕሮጀክቶች መሬት በምደባ እንዲተላለፍ ማድረግ፣

ክፍል ሁለት
የኢንቨስትመንት ዘርፍ አይነቶች ፤ መሬት መጠን፣ የካፒታል እና የሥራ ዕድል መጠን አወሳሰን

6. የኢንቨስትመንት ዘርፎች

የኢንቨስትመንት ዘርፎች በካፒታል መጠን፣ በመሬት መጠን እና ፕሮጀክቶቹ ሊፈጥሩት በሚገባው ቋሚ የሥራ ዕድል መጠን በሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና ዘርፎች የሚቀመጡ ይሆናል፦

1) የግብርና ዘርፍ

በግብርናዉ ዘርፍ የሚከተሉት ዋና ዋና ንዑስ ዘርፎች ተካተዋል፦

1. የእርሻ ልማት ዘርፍ በስሩ ዓመታዊ ሰብሎች ልማት፣ የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ልማት፣ የቋሚ ተክሎች ልማት፣ አትክልና ፍራፍሬ ልማት እና የደን ልማት ዘርፎችን ይይዛል።
2. የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ በስሩ የሚከተሉትን የሚያካትት ሲሆን እነዚህም የቤት እንስሳት ልማት እና የዱር እንስሳት ልማት ዘርፎችን ይይዘል።

2) የኢንዱስትሪ ዘርፍ

በዋናነት በኢንዱስትሪ ዘርፍ ሊካተቱ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰቡ ዘርፎች በዋና ዋና እና በስራቸው በሚኖሩ ዝርዝር የኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚከተሉት ናቸዉ፦

1. የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ፣
2. የመጠጥ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ፣
3. የጨርቃ ጨርቅ ምርት እና የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪ፣
4. የቆዳና ተያያዥ ምርቶች ኢንዱስትሪ፣
5. እንጨትና እንጨት ተዋጽኦ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
6. የወረቀት እና የወረቀት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
7. የህትመት ኢንዱስትሪ፣
8. የፕላስቲክ፣ የጫማ ቀለምና የመሳሰሉት ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
9. የኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
10. የመድኃኒት ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
11. የጎማ ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
12. የብረት ማዕድን ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ፣
13. የብረት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ ናቸዉ፡፡

3) የአገልግሎት ዘርፍ፡-

በአገልግሎት ዘርፍ ሊሰማሩ ይችላሉ ተብለው የሚታሰቡ በሚከተሉት ዋና ዋና ዘርፎች ተቀምጠዋል፡-

1. የሆቴል እና የቱሪዝም መዳረሻዎች አገልግሎት ዘርፍ፣
2. የጤና አገልግሎት ዘርፍ፣
3. የትምህርት ዘርፍ፣
4. የሪልስቴትና የገበያ ማዕከል

7. የኢንቨስትመንት መሬት መጠን አወሳሰን

በየዘርፉ የተዘረዘሩ በርካታ ፕሮጀክቶች ያሉ ቢሆንም ለአብነት እንዲሆኑ ከየዘርፉ የሚከተሉት ማሳያዎች ተቀምጧል፡-

1) አብነት አንድ፣ ግብርና

1. የእርሻ ንዑስ ኢንቨስትመንት

Ce/Bi/R/S/Investment & Industry Development Bureau

ለእርሻ ንዑስ ኢንቨስትመንት ዘርፍ የመሬት መጠንን ለመወሰን የሚከተሉት ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ይሆናል፡-

1. ለእርሻ ሥራ አገልግሎት የሚውል መሬት፣
2. በእርሻ መካከል ሊኖር የሚችል መተላለፊያ መንገዶች የሚውል ቦታ፣
3. ለምርት ማከማቻ የሚውል መጋዘን መስሪያ ቦታ፣
4. የአስተዳደር ህንፃ (የካምፕ ግንባታ አገልግሎት) መስሪያ ቦታ፣
5. ለዘር እና መድኃኒቶች (ግብዓቶች) ማከማቻ መጋዘን እና የመሳሰሉት።

2. የእንስሳት ንዑስ ኢንቨስትመንት

ለእንስሳት ኢንቨስትመንት ንዑስ ዘርፍ የመሬት መጠንን ለመወሰን የሚከተሉት ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ይሆናል፡-

1. የእንስሳት መጠለያ ቤቶች መገንቢያ ቦታ፣
2. የእንስሳት ማናፈሻ ቦታ፣
3. የእንስሳት ውሃ ማጠጫ
4. የመኖ ማከማቻ ቦታ፣
5. ለሠራተኞች መጠለያ መስሪያ ቦታ፣
6. የጥበቃ ማማዎች የሚያርፉበት ቦታዎች፣
7. የእንስሳት ህክምና አገልግሎት መስጫ ቦታ፣
8. የአስተዳደር ህንፃ መገንቢያ ቦታ፣
9. የምርት ማጠራቀሚያና ማቀነባበሪያ ቦታ፣
10. እንደአስፈላጊቱ ወይም እንደፕሮጀክቱ ዓይነት የመኖ ማምረቻ ቦታ የመሳሰሉት ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ይሆናል።

2) አብነት ሁለት፡-ኢንዱስትሪ

የኢንዱስትሪ ዘርፍ በዓይነቱም ይሁን በባህሪው በርካታ ንዑስ ዘርፎችን የያዘ መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም የኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ዘርፍ የመሬት መጠንን ለመወሰን የሚከተሉት ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ይሆናል፦

1. የማምረቻ ፋብሪካውን ሊያሳርፍ የሚችል ቦታ፣
2. የፋብሪካ ግብዓት ማስቀመጫ መጋዘን ቦታ፣
3. የምርት ማከማቻ መጋዘን ቦታ፣
4. የአስተዳደር ህንፃ መገንቢያ ቦታ፣
5. ምርት ለመጫንና ግብዓት ለማውረድ የሚገቡና የሚወጡ ተሽከርካሪዎች ማስተላለፊያ ቦታ፣
6. የፋብሪካው ተሽከርካሪዎች ማቆሚያ ቦታ የመሳሰሉት ጉዳዮች በቦታ መጠን አወሳሰን ላይ ከግምት ይገባሉ።

3) አብነት ሦስት፦ አገልግሎት ዘርፍ

ለአገልግሎት ኢንቨስትመንት ዘርፍ የመሬት መጠንን ለመወሰን የሚከተሉት ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ይሆናል፦

1. ለአገልግሎት የሚውሉ ህንፃዎች ማነባታ ቦታ፣
2. ለመኪና ፓርኪንግ ቦታዎች፣
3. የመዝናኛ ቦታዎች፣(ውኃ ዋና፣ስፖርት ማዘውተሪያ፣ የህፃናት መጫወቻዎች)፣
4. መጋዘን፣ ላውንደሪ፣ ኪችን ቦታዎች፣
5. አስተዳደራዊ ህንፃ (እንደ አስፈላጊነቱ)፣
6. የፍሳሽ ማስወገጃ ቦታዎች፣
7. መተላለፊያ ክፍት ቦታዎች እና ሌሎች ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ይሆናል።

8. የኢንቨስትመንት ካፒታል አወሳሰን

1) በሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በቅድሚያ ለፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የመሬት መጠን እንዲሁም መነሻ ካፒታል ተወስኗል። በተጨማሪም ለፕሮጀክቱ ከተቀመጠው ዝቅተኛ የመሬት መጠን በላይ ለሚጠይቅ ባለሀብት ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ካሬ ሜትር የተቀመጠውን አማካይ የገንዘብ መጠን ሲያቀርብ ተጨማሪ መሬት የሚያገኝ ይሆናል።

ማለትም፡-ዝቅተኛ የኢንቨስትመንት መነሻ ካፒታል መጠን እንደየ ኢንቨስትመንት ዓይነት የመሬቱ መጠን ይወሰናል።

ስሌቱም K + (N x Av) = ዝቅተኛ የኢንቨስትመንት መነሻ ካፒታል ይሆናል።

"K" ማለት ለፕሮጀክቱ ዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ የኢንቨስትመን ካፒታል በብር ማለት ነው።

"AV" ማለት የፕሮጀክቱ አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ) ማለት ነው።

"N" ማለት ለኢንቨስትመንቱ የተዘጋጀው የመሬት መጠን ሲቀነስ ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ ማለት ነው።

2) በኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚቀርቡ ፕሮጀክቶች በቅድሚያ ለፕሮጀክቶቹ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የመሬት መጠን እንዲሁም መነሻ ካፒታል በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ሥር በተመለከተዉ ሠንጠረዥ መሠረት ይፈፀማል። በተጨማሪም ለኢንዱስትሪው ከተቀመጠው ዝቅተኛ የመሬት መጠን በላይ ለሚጠይቅ አልሚ ባለሀብት ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ካሬ ሜትር የተቀመጠውን አማካይ የገንዘብ መጠን ሲያቀርብ ተጨማሪ መሬት የሚያገኝ ይሆናል።

9. ኢንቨስትመንቱ ሊፈጥር የሚገባው ዝቅተኛ የሥራ ዕድል ፈጠራ መጠን በተመለከተ

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ሊፈጥሩ የሚችሉትን ዝቅተኛ የሥራ ዕድል ከመወሰን ጋር በተያያዘ የሚከተሉት የተለያዩ ጉዳዮች ታሳቢ ይደረጋሉ።

1) ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር

ዝቅተኛ ቋሚ የሥራ ዕድል ለመፍጠር መሬት በምደባ ለመስጠት እንዲቻል በተዘጋጀው መስፈርት (ስታንዳርድ) መሠረት አንድ ፕሮጀክት ሊፈጥር የሚችለውን ዝቅተኛ የሥራ ዕድል በካፒታል መጠን ይሆናል። በሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ወደ ሥራ ለመግባት የሚደራጁ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከቋሚ ሥራ ዕድል ፈጠራ አንጻር ከዝቅተኛው የካፒታል መጠን በመነሳት እያደገ የሚሄድ ስሌት ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል። ይህም ከዝቅተኛው የካፒታል መጠን በመነሳት እያደገ የሚሄድ ስሌት በሚከተለው ሁኔታ ይሆናል።

1. ከብር 8,320,000 እስከ ብር 25,000,000 የሚፈጥረው ዝቅተኛው ቋሚ የሥራ ዕድል 20 ሰው እንዲሆን፣

2. ከብር 25,000,001 እስከ ብር 50,000,000 የሚፈጥረው ዝቅተኛው ቋሚ የሥራ ዕድል 25 ሰው እንዲሆን፣

3. ከብር 50,000,001 እስከ ብር 75,000,000 የሚፈጥረው ዝቅተኛው ቋሚ የሥራ ዕድል 30 ሰው እንዲሆን፣

4. ከብር 75,000,001 እስከ ብር 100,000,000 የሚፈጥረው ዝቅተኛው ቋሚ የሥራ ዕድል 35 ሰው እንዲሆን፣

5. ከብር 100,000,001 ብር በላይ ሊፈጥር የሚችለው ዝቅተኛው ቋሚ የሥራ ዕድል ከዚህ በላይ በተቀመጠው ስሌት መሠረት የሰው ቁጥሩም እየተሰላ የሚሄድ ይሆናል፡፡

6. ቋሚ የሥራ ዕድል ስለመፈጠሩ ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በተመለከተ፡-

   ሀ. ድርጅቱ/ ባለሀብቱ ከሠራተኞቹ ደመወዝ እየቆረጠ ለመንግስት ገቢ ያደረገበት የታክስና ግብር ማስረጃዎች፣

   ለ. ድርጅቱ/ ባለሀብቱ ለግል ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና በየወሩ ከደመወዛቸው እየቀነሰ የሚያስገባው የጡረታ መዋጮ ማስረጃ እንደመከታተያ ማስረጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡

7. ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ስለመፈጠሩ ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን በተመለከተ፡-

   ሀ. ጊዜያዊ የሥራ ዕድል መፍጠርን በተመለከተ ድርጅቱ ወይም አልሚው አካል ለራሱ ጥቅም ሲል ከገበያ ላይ አፈላልጎ የሚያሰራው በመሆኑ ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጠራ መጠን እንደ ፕሮጀክቱ ስፋት እና ሁኔታ እየታየ በቢሮ የሚወሰን ይሆናል፡፡

8. የቴክኖሎጂ ሽግግር ሁኔታ፡-

   ሀ. ፕሮጀክቱ በተሰማራበት ዘርፍና የሥራ መስክ መነሻ በማድረግ ፕሮጀክቱ በሚገኝበት አከባቢ ለሚገኝ ማህበረሰብን ሊጠቅም የሚችል በተለይም በአሰራር ዘረያ ዕመርታዊ ለውጥ፣ ምርትና ምርታማነት ማሳደግ

የሚችሉና በጥቅሉ የዘመነ፣ አሰራርን የሚያቀላጥፉ ቴክኖሎጂዎች ታሳቢ ተደርጓል፡፡

ለ. ከቴክኖሎጂ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በተለይ በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ አልሚዎች ፕሮጀክቱ በሚገኝበት አካባቢ ለሚገኘዉ አርሶ እና አርብቶ አደር የዕውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ምርጥ የሰብል ዘሮች እና ችግኞችን ማቅረብ፣ የእርሻ ማሳ ዝግጅት፣ ምርጥ ዘር አጠቃቀም፣ የምርት አሰባሰብ ሂደት ላይ ተሞክሮ ማካፈል፣ የሰብል እንክብካቤና ጥበቃ ሥራዎች ላይ እና የአካባቢ ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን ላይ ግንዛቤ መፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሐ. በአርሶ እና አርብቶ አደር አካባቢ የሚሰማሩ ድርጅቶች የአካባቢዉ ማህበረሰብ ፍላጎት ታሳቢ ባደረገ መንገድ ማሽነሪዎች አጠቃቀም ላይ በማሰልጠን እንዲሳተፉ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

10. የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ሁኔታዎች፡-

1) በክልሉ ውስጥ በመስኖ ማልማት በማይቻልባቸው አካባቢዎች ብቻ በዝናብ መልማት ለሚችሉ ሰብሎች የኢንቨስትመንት መሬት የሚሠጥ ይሆናል፡፡
2) በክልሉ ውስጥ መስኖ መጠቀም በሚቻልባቸው አካባቢዎች በዝናብ ለማልማት ጥያቄ ለሚያቀርብ ባለሃብት የኢንቨስትመንት መሬት አይፈቀድም፡፡
3) ለአምራች ኢንዱስትሪዎች በተለይ የአርሶ አደሩን ምርት በግብዓትነት የሚጠቀሙ እና ብዙ የስራ እድል የሚፈጥሩ ከሆኑ ለኢንዱስትሪ በተለዩ አካባቢዎች ተገቢው ድጋፍ ተደርጎላቸው ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡
4) በወረዳ ደረጃ የተቋቋመው/የሚቋቋመው የኢንቨስትመንት ካውንስል ከዞን ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያ ጋር በቅንጅት በመስራት በወረዳው ለሚቀርቡ አዳዲስ የኢንቨስትመንት ነክ ስራዎችን ያስፈፅማል፡፡
5) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት እንዲተገበር ከመፈቀዱ በፊት ከአካባቢ ጋር ተስማሚ መሆኑን ወይም በአካባቢ ላይ የሚያደርሰው ተፅዕኖ ካለ የማረሚያ አማራጭ መቅረብ አለበት፡፡

6) ማንኛውም መሬት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት እንዲፈቀድ የውሳኔ ሀሳብ ወደ ክልል ከመላኩ በፊት ዞኑ/ ልዩ ወረዳው መሬቱ ከሶስተኛ ወገን ይገባኛል ጥያቄ ነፃ መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለበት፡፡

7) የተፈቀደውን የገጠር መሬት መጠን የሚያሳይ X-Y Coordinate በGPS ተሰርቶ በዞኑ በኩል ከፕሮጀክት ፕሮፖዛል ጋር መቅረብ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በከተማ ላይ የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች በከተማ ልማት መምሪያ በኩል የተዘጋጀውን መሬት በጋይድ ማፕ ተደግፈው መቅረብ አለባቸው፡፡

8) መሬት እንዲፈቀድለት የጠየቀ ባለሀብት በዚህ መመሪያ የተገለፀው የካፒታል አቅም ማሳያ ዝቅተኛው ብር መጠን ቢያንስ የፕሮጀክቱን ካፒታል 30% ያለው(clothing balance) የቅርብ ጊዜ የ6 ወር ገቢና ወጪ እንቅስቃሴ ያጠቃለለ ሆኖ የመጨረሻው ተንባቢ/ቀሪ ብር ስለመሆኑ ከባንክ ማረጋገጫ ሲያቀርብ በደብዳቤ ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

9) የፕሮጀክቱ ባለቤትነት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሆነ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ እና ከባንክ የሚቀርበው 30% የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን መነሻ ካፒታል በማህበሩ ስም መቅረብ አለበት፡፡ ማህበሩ ከተመሠረተ ስድስት (6) ወር ያልሞላው ከሆነ በስሙ 30% የፕሮጀክት ፕሮፖዛሉን መነሻ ካፒታል በደብዳቤ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

10) እንደ አስፈላጊነቱ የባለሀብቱን የኋላ የቢዝነስ ፕሮፋይል የንግድ ሥራ ፈቃድ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ፣ ለዞኑ/ ክልሉ ያደረገው ማህበራዊ አበርክቶ ወ.ዘ.ተ...) እና ባለሃብቱ ዲያስፖራ ከሆነ ዲያስፖራነቱን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በግልፅ ማሳየት የሚችል ዝርዝር መግለጫ በዞኑ በኩል መቅረብ ይኖርበታል፡፡

11) የዞን/የልዩ ወረዳ አስተዳደር ከወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ጋር በጋራ የመሬት አስተዳደር ህጎችን ጠብቆ ለኢንቨስትመንት የሚውል መሬት በመለየት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡ መሬቱን ለይቶ ካዘጋጀ በኋላ ባለሀብት በመጋበዝ የላቀ ፋይዳ ያለው የፕሮጀክት ሀሳብ ያቀረበ እና የተሻለ የመስራት አቅም ያለው ባለሀብት ይመርጣል፡፡

12) የዞን/የልዩ ወረዳ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያ ወይም ጽ/ቤት ከወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ወይም ከከተማ አስተዳደሩ የተላኩለትን ፕሮጀክቶች በፍጥነት በገምጋሚ ኮሚቴ አማካኝነት ተገምግሞ በዞኑ/ በልዩ ወረዳ ወይም

በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ አጽድቆ የውሳኔ ሃሳብ ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ይልካል፡፡

13) ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትም ፕሮጀክቱ በኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በተቋቋመው ገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ ለክልሉ ለካቢኔ የውሳኔ ሃሳብ እንዲቀርብ ለኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ከዞን/ ከልዩ ወረዳ አስተዳዳር ጽ/ቤት የቀረቡለትን ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎች ለኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ይልካል፡፡

14) ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትም ከኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የቀረቡለትን የውሳኔ ሀሳብ ለክልሉ ካቢኔ በማቅረብ ያስወስናል፤ ውሳኔውንም ለዞኑ/ ለልዩ ወረዳ ጽ/ቤት አስተዳደር ያሳውቃል፡፡

15) ባለሀብቱ በአካል መገኘት ሳያስፈልገው ፕሮጀክቱን መስራት ለሚፈልግበት ዞን ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያ ወይም ለዞኑ አስተዳደር በሚያስቀምጠው (plat form) አማራጭ መንገድ (On line) መላክ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ክልሉ በሚዘረጋው ፕላት ፎርም (plat form) መሰረት ዞኑም ፕሮጀክቱን ከውሳኔ ሀሳብ ጋር (On line) ወደ ክልል መላክ ይችላል፤ በመገምገሚያ መስፈርትነት የተጠቀሱ ጉዳዮችን ያላሟላ ፕሮጀክት ወደ ክልል መላክ የለበትም፡፡

16) ማንኛውም ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት የግንባታ ሂደቱን ጨርሶ ወደ ማምረት/ አገልግሎት መስጠት ሲሸጋገር ከኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ክትትልና ድጋፍ በተጨማሪ የሚመለከተው ሴክተር መ/ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ከቢሮው ጋር በመተባበር የክትትልና ድጋፍ ሥራን ያከናውናል፡፡

17) ፕሮጀክቱ ለክልል ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ በቀረበ ባጠረ ጊዜ ውስጥ ተገምግሞ ለርዕሰ መሥተዳድር ጽ/ቤት መቅረብ አለበት፡፡

18) ፕሮጀክቱ በክልሉ ካቢኔ ከጸደቀ በኋላ የታችኛው መዋቅር (ዞን/ል/ወረዳ) ባለሃብቱ መሬቱን ለመረከብ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ባጠረ የሥራ ቀናት ውስጥ መሬቱን ማስረከብ ይጠበቅበታል፡፡

11. በልዩ ሁኔታ ስለሚታዩ ፕሮጀክቶች

1) ከርዕሰ መስተዳድር በኩል ከታችኛው መዋቅር የሚቀርቡ አዳዲስ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የቢሮ ገምጋሚ ኮሚቴው ተገምግመው በኮሚቴ ደረጃ መግባባት

ባልተቻለባቸው ጉዳዮች የቢሮ ኃላፊና የኢንቨስትመንት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ሃሳብ ይወሰዳል።

2) በመስፈርቱ/ በስታንዳርድ ከተዘረዘሩት ውጭ የሚመጡ ፕሮጀክቶች በመስፈርቱ/ ስታንዳርድ ላይ ከግብርና፣ ኢንዱስትሪ እና አገልግሎት ዘርፍ አንፃር የተዘረዘሩ በርካታ ፕሮጀክቶች ቢኖሩም በተለያዩ ምክንያቶች ለየት ያለ ስም ወይም ባህሪ ያላቸው ፕሮጀክቶች ከመጡ በመስፈርቱ/ በስታንዳርዱ ውስጥ ለመጣው ፕሮጀክት ተቀራራቢነት ያላቸው ፕሮጀክቶች መሆናቸው ታይተው እንዲስተናገዱ የሚደረግ ሲሆን ተቀራራቢነት የሌላቸዉ ፕሮጀክቶች ከመጡ የክልሉ መንግስት ፕሮጀክቱ ለአካባቢዉ ከሚሰጠዉ ፋይዳ አንፃር የሚወሰን ይሆናል።

12. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ልዩ ውሳኔ ስለሚሰጥባቸው ፕሮጀክቶች

ይህ መስፈርት ወደ ክልሉ በሚመጡ ባለሀብቶች የሚቀርቡ ፕሮጀክቶችን ተመልክቶ ለመገምገም የተዘጋጀ ቢሆንም የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ልዩ ጠቀሜታ አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ፕሮጀክቶች በልዩ ሁኔታ ተመልክቶ መወሰን ይችላል።

13. ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል የመሬት እና የካፒታል መጠን መስፈርት

1. ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል የመሬት እና ካፒታል መጠን መስፈርት በዚህ መመሪያ መሰረት ይፈጸማል።
2. በንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል የመሬት እና ካፒታል መጠን መስፈርት አሰጣጥ የዚህ መመሪያ አባሪ ሰንጠረዦች መሰረት ይከናወናል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14. የቅሬታ አቀራረብ

በአዲስ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት አሰጣጥ ሂደት ላይ በዞን/ልዩ ወረዳው ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት መምሪያ /ጽ/ቤት ወይም በክልሉ ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አሰራር ላይ ቅሬታ ያለው አካል ለክልሉ/ ርዕሰ መስተዳደር ጽ/ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

15. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸዉ ህጎች

ማንኛዉም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ዉስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረዉም፡፡

16. መመሪያዉን ስለመሻሻል

1) ቢሮዉ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ ይሄንን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡
2) ቢሮው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1) መሰረት መመሪያውን ሲያሻሽል ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ማሳወቅ እና ማስመዝገብ አለበት፡፡

17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ማኔጅመንት ኮሚቴ ጸድቆ በክልሉ ፍትህ ቢሮ ከተመዘገበበት ከሰኔ.......ቀን/2018 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ቡታጅራ

ሰኔ /2018 ዓ.ም

አባስ መሀመድ (ዶ/ር)

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

ኢንቨስትመንትና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ

ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አገልግሎት የሚውል የመሬት መጠን፣ የኢንቨስትመንት ካፒታል እና የሥራ ዕድል ፈጠራ መስፈርትን የሚያሳይ ሠንጠረዥ

1. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፍ መስፈርት/ስታንዳርድ፡-

1.1 በከተማ የሚተገበር ኢንዱስትሪ

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ለኢንቨስትመንት ካፒታል (ብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ለኢንቨስትመንት ካፒታል (ብር)
1	የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ					
1.1	ዘመናዊ የእንስሳት ማረጃ ቄራ- ለከብት፣ለበግ፣ ለፍየል	5,000	15,000	10,062	50,310,000	150,930,000
1.2	የአሳ ስጋ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	1,000	3,000	30,186	30,186,000	90,558,000
1.3	የዶሮና የመሳሰሉ እንስሳት ስጋ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	1,000	3,000	30,186	30,186,000	90,558,000
1.4	የአትክልትና ፍራፍሬ ውጤቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	2,000	3,000	18,416	36,831,600	55,247,400
1.5	የምግብ ዘይት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	4,000	6,000	13,260	53,040,000	79,560,000
1.6	የእህል ዱቄት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	2,500	3,000	11,700	29,250,000	35,100,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
1.7	የፓስታ፣ የመኮሮኒ፣ የብስኩት እና የህጻናት ምግብ ማምረቻ ኢ/ራ	2,500	3,000	15,600	39,000,000	46,800,000
1.8	ዱቄትና የመኮሮኒ፣ የብስኩት እና የህጻናት ምግብ ማምረቻ ኢ/ራ	7,500	10,000	15,600	46,800,000	78,000,000
1.19	የከረሜላ፣ የቾኮሌትና የማስቲካ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	500	1,000	48,750	24,375,000	48,750,000
1.1	ቡና ቆልቶ ፈጭቶ የማሸግ ኢንዱስትሪ	500	1,000	32,500	16,250,000	32,500,000
1.11	ቅመማ ቅመም ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	500	1,000	32,500	16,250,000	32,500,000
1.12	የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	3000	3000	13,000	39,000,000	65,000,000
1.13	ደረቅ ቡና ማበጠሪያ ኢንዱስትሪ	5000	10,000	3,093	15,463,500	30,927,000
1.14	የማር ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	500	1,000	16,640	8,320,000	16,640,000
1.15	የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	3,000	5,000	13,000	39,000,000	65,000,000

2	የመጠጥ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ					
2.1	የቢራ መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካ	20,000	40,000	65,000	1,300,000,000	2,600,000,000
2.2	የአልኮል/ አረቂ መጠጥ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	65,000	325,000,000	650,000,000
2.3	ለስላሳ መጠጥ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	40,000	14,300	286,000,000	572,000,000
2.4	የታሸገ የመጠጥ ውሃ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	11,050	120,000,000	500,000,000
2.5	የብቅል ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	10,000	18,000	13,000	130,000,000	234,000,000
3	የጨርቃጨርቅ ምርትና ልብስ ስፌት ፋብሪካ					
3.1	ጥጥ መዳመጫ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	11,271	56,355,000	112,710,000
3.2	ጨርቃጨርቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	30,000	26,000	390,000,000	650,000,000
3.3	ጋርሜንት/የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪ	5,000	15,000	13,000	65,000,000	195,000,000
3.4	የባንዴጅ፣ የዳይፐርና መሰል ጨርቆችን አምራች ኢንዱስትሪ	1,000	2,000	26,000	26,000,000	52,000,000
3.5	የፎጣ፣ካልሲ፣ጋንትና የመሳሰሉትን ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,000	26,000	26,000,000	52,000,000
3.6	የሹራብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,000	24,960	24,960,000	49,920,000
3.7	የቤት ንጣፍ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,500	3,000	43,333	64,999,350	129,998,700
3.8	የልብስ ቁሳቁስ ዚፕ ፣አዝራርና የመሳሰሉት ማምረቻ ማሽን	500	1,000	33,280	16,640,000	33,280,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
3.9	የስፖርት ትጥቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,000	32,500	32,500,000	65,000,000
3.1	የብርድ ልብስ ማምረቻ ኢንዱትሪ	1,000	2,000	48,750	48,750,000	97,500,000
3.11	የሹራ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,000	48,750	48,750,000	97,500,000
4	የሌዘርና ተያያዥ ምርቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
4.1	የቆዳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	5,000	1,0000	14,040	70,200,000	140,400,000
4.2	የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2000	26,000	26,000,000	52,000,000
5	የእንጨትና የእንጨት ተዋፅኦ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
5.1	የቺፕ ዉድ፣ የፋይበሊስት ፣ ፕሊይዉድ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	30,000	13,260	66,300,000	132,600,000
5.2	የቺፕ ዉድ፣ የፋይበሊስት ፣ ፕሊይዉድ ውጤቶችን ተጠቅሞ ፈርኒቸር ማምረቻ ኢንዱስትሪ	2,500	5,000	20,800	52,000,000	104,000,000
5.3	የእስቲኪኒ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	200	500	52,000	10,400,000	26,000,000

6	የወረቀትና የወረቀት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
6.1	የወረቀት ፐልፕ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	7,000	15,000	19,500	136,500,000	292,500,000
6.2	የወረቀት ሪሳይክሊንግ ኢንዱስትሪ	1,500	2,500	26,000	39,000,000	65,000,000
6.3	የመፀዳጃ ቤት ወረቀት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,500	2,500	26,000	39,000,000	65,000,000
7	የህትመት ኢንዱስትሪ					
7.1	የመፅሃፍ ህትመት፣ የጋዜጣና የብሮሽር ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,500	3,000	22,100	33,150,000	66,300,000
6.	የጎማና የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
8.1	የፕላስቲክ (PVC) እና (PP) ፕላስቲክ የሚጣ ቀለምና የመሳሰሉት ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	32,500	32,500,000	97,500,000
8.2	የፕላስቲክ ከረጢት፣ ጆንያና የመሳሰሉት የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	32,500	32,500,000	97,500,000
8.3	የኤሌክትሪክ ኮንዳዩትና ሌሎች ተመሳሳይ ቁሳቁሶችን ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	27,950	27,950,000	83,850,000
9	የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ					
9.1	ፀረ-ተባይና ፀረ- አረም ኬሚካል ማምረቻ	3,000	5,000	32,500	97,500,000	162,500,000
9.2	የቀለም፣ የሙጫና የቫርኒሽ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	3,000	5,000	26,000	78,000,000	130,000,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/አ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)
9.3	የሳሙና፣ የዲተርጀንት፣ የሽታና ሌሎች የማፅጃ ኬሚካሎች ኢንዱስትሪ	3,000	5,000	26,520	79,560,000	132,600,000
9.4	የኮስሞቲክስ ኢንዱስትሪ	500	1,000	39,000	19,500,000	39,000,000
9.5	የፎም ዉጤቶች ኢንዱስትሪ	5,000	15,000	26,520	79,560,000	132,600,000
9.6	የክብሪትና የሰንደል ማምረቻ ኢንዱስትሪ	500	1000	39,000	19,500,000	39,000,000
9.7	የኦክሲጂን ፣ የሃይድሮጅን እና ሌሎች ጋዞች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,000	29,250	29,250,000	58,500,000
10	የመድሃኒት ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
10.1	የመድሃኒት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	26,000	130,000,000	260,000,000
11	የጎማና የፕላስቲክ ዉጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
11.1	የመኪና ጎማ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	6,800	26,000	130,000,000	176,800,000
12	የብረት ማዕድን ዉጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
12.1	የመስታወትና የመስታወት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	19,934	199,342,000	299,000,000
12.2	የብሎኬት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	3,000	5,000	15,600	36,000,000	60,000,000
12.3	የሴራሚክስ ዉጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	18,200	182,000,000	273,000,000
12.4	የማርብል፣ የግራናይት፣ የላይምስቶን ድንጋይ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	21,667	216,671,000	325,006,500
12.5	የብረት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	17,334	173,342,000	260,013,000

13	የብረት ዉጤቶች ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ					
13.1	የሚስማር፣ የቆርቆሮ፣ የአጥር ሽቦ እና የመሳሰሉ ዕቃዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	39,000	78,000,000	117,000,000
13.2	የግብርና ማሽኖች (ኮምባይነር፣ትራክተር...) ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	30,000	26,000	260,000,000	780,000,000
13.3	የእርሻ መሳሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	3,000	5,000	32,500	65,000,000	97,500,000
13.4	የመኪና ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	26,000	780,000,000	1,040,000,000
13.5	የሳይክልና የሞተርሳይክል ማምረቻ ኢንዱስትሪ	4,000	8,000	39,000	78,000,000	117,000,000
13.6	የኤስታብላይዘር፣ የኤሊቬተር፣ የቦይለር፣ የትራንስፎርመር፣ የጀነሬተርና UPS ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	39,000	195,000,000	390,000,000
13.7	የላቦራቶሪና የሃኪም ቤት ቁሳቁሶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	7,000	39,000	78,000,000	117,000,000
13.8	የኮሚኒኬሽን፣ የመብራት ገመድና ቁሳቁሶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	4,000	6,000	26,000	78,000,000	130,000,000
13.9	የማሰ፣ የቶርኪ፣ ውሃ ማሸጊያ ፕላስቲክ በርሜል እና ክዳን እና የመሳሰሉትን ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	7,000	22,100	44,200,000	66,300,000

Ca/Et/R/Investment & Industry Development Bureau

2.1. በገጠር የሚተገበር ኢንዱስትሪ

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ በኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ በኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
1	የምግብ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ					
1.1	ዘመናዊ የእንስሳት ማረጃ (ቄራ)/ለከብት፣ለበግ፣ለፍየል	10,000	30,000	5,031	50,310,000	150,930,000
1.2	የአሳ ስጋ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	1,000	5,000	18,112	30,186,000	90,558,000
1.3	የዶሮና የመሳሰሉ እንስሳት ስጋ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	1,000	5,000	18,112	30,186,000	90,558,000
1.4	የአትክልትና ፍራፍሬ ውጤቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	2,000	5,000	11,050	36,831,600	55,247,400
1.5	የምግብ ዘይት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	4,000	10,000	7,956	53,040,000	79,560,000
1.6	የእህል ዱቄት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	2,500	5,000	7,020	[illegible]50,000	35,100,000
1.7	የፓስታ፣ የመኮሮኒ፣ የብስኩት እና የህጻናት ምግብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	9,360	39,000,000	46,800,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በአራ ሜትር (ብር/ለሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)
1.8	የስኳር ፋብሪካ	30,000	50,000	8,680	310,017,500	434,005,000
1.9	የከረሜላ፣ የቾኩሌትና የማስቲካ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	500	3,000	16,250	24,375,000	48,750,000
1.10	ቡና ቆልቶ ፈጭቶ የማሸግ ኢንዱስትሪ	500	3,000	10,833	16,250,000	32,500,000
1.11	ቅመማ ቅመም ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	10,00	1,500	21,666	16,250,000	32,500,000
1.12	የወተት ውጤቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	6,500	39,000,000	65,000,000
1.13	እሸት ቡና መፈልፈያ ኢንዱስትሪ	20,000	30,000	972	19,448,000	29,172,000
1.14	ደረቅ ቡና ማበጠሪያ ኢንዱስትሪ	5,000	15,000	2,062	15,463,500	30,927,000
1.15	የማር ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	5,547	8,320,000	16,640,000
1.16	የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	5,850	39,000,000	58,500,000

2	የመጠጥ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ					
2.1	የቢራ መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካ	20,000	60,000	43,334	1,300,000,000	2,600,000,000
2.2	የአልኮል/ ሀረቂ መጠጥ ማምረቻ ለኢንዱስትሪ	5,000	20,000	32,500	325,000,000	650,000,000
2.3	ለስላሳ መጠጥ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	60,000	9,533	286,000,000	572,000,000
2.4	የታሸገ የመጠጥ ውሃ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	30,000	3,683	120,000,000	500,000,000
2.5	የብቅል ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	10,000	25,000	9,360	130,000,000	234,000,000
3	የጨርቃጨርቅ ምርትና ልብስ ስፌት ፋብሪካ					
3.1	ጥጥ መዳመጫ ኢንዱስትሪ	10,000	20,000	4,335	56,355,000	112,710,000
3.2	ጨርቃጨርቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	40,000	12,560	390,000,000	650,013,000
3.3	ጋርሜንት/የልብስ ስፌት ኢንዱስትሪ	10,000	20,000	7,500	65,000,000	195,000,000
3.4	የጣንዱሽ ፣ የዳይፐርና መሰል ጨርቆችን አምራች ኢንዱስትሪ	1,000	2,500	16,000	[illegible]	52,000,000
3.5	የፎጣ፣ካልሲ፣ፓንትና የመሳሰሉትን ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,200	16,000	[illegible]	52,000,000
3.6	የሹራብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,500	15,360	24,960,000	49,920,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ
3.7	የቤት ንጣፍ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,500	5,000	26,000	64,999,350	130,000,000
3.8	የልብስ ቁሳቁስ ዚፕ ፣አዝራርና የመሳሰሉት ማምረቻ ማሽን	300	5,000	6,656	16,640,000	33,280,000
3.9	የስፖርት ትጥቅ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	5,000	13,000	32,500,000	65,000,000
3.1	የብርድ ልብስ ማምረቻ ኢንዱትሪ	1,000	5,000	19,500	48,750,000	97,500,000
3.11	የሸራ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	5,000	19,500	48,750,000	97,500,000
4	የሌዘርና ተያያዥ ምርቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
4.1	የቆዳ ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ	5,000	15,000	9,360	70,200,000	140,400,000
4.2	የቆዳ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,500	20,800	20,800,000	52,000,000
5	የኬሚካልና የኬሚካል የተዋፅኦ ዉጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
5.1	የፔፕ ዉድ፣ የፋይበርስት ፣ ፓርቲክል ቦርድ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	88,400	66,300,000	132,600,000
5.2	የ ፕላስቲክ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	200	5000	26,000	10,400,000	26,000,000
6	የወረቀትና የወረቀት ዉጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
6.1	የወረቀት ፐልፕ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	14,625	[illegible]	292,500,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል
6.2	የወረቀት ሪሳይክሊንግ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	10,400	39,000,000	65,001,300
6.3	የመፀዳጃ ቤት ወረቀት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	21,667	39,000,000	65,001,300
7	የህትመት ኢንዱስትሪ					
7.1	የመፅሃፍ ህትመት፣የጋዜጣና የብሮሸር ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	7,000	13,260	33,150,000	66,300,000
8	የራበርና የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
8.1	የፕላስቲክ (PVC) እና (PP) ፕላስቲክ የቧንቧ ቀለምና የመሳሰሉት ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	19,500	32,500,000	97,500,000
8.2	የፕላስቲክ ከረጢት፣ ጆንያና የመሳሰሉት የፕላስቲክ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	7,000	10,000	19,500	32,500,000	97,500,000
8.3	የኤሌክትሪክ ኮንዳክትና ሌሎች ተመሳሳይ ቁሳቁሶችን ማምረቻ ኢንዱስትሪ	7,000	10,000	16,770	27,950,000	83,850,000
9	የኬሚካል ውጤቶች ኢንዱስትሪ					
9.1	የአፈር ማዳበሪያ ማቀነባበሪያ	30,000	[illegible]	5,850	175,500,000	292,500,000
9.2	ፀረ-ተባይና ፀረ- አረም ኬሚካል ማምረቻ	5,000	10,000	16,250	97,500,000	162,500,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በሄ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በሄ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (በብር/ሜ²)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ለ/ኢንቨስትመንት ካፒታል	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ለ/ኢንቨስትመንት ካፒታል
9.3	የቀለም ፣የሙጫና የቫርኒሽ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	13,000	78,000,000	130,000,000
9.4	የሳሙና፣የዲተርጀንት፣የሽቶና ሌሎች የማፅጃ ኬሚካሎች ኢንዱስትሪ	5,000	10,000	13,260	79,560,000	132,600,000
9.5	የኮስሞቲክስ ኢንዱስትሪ	500	1,000	26,000	19,500,000	39,000,000
9.6	የፎም ዉጤቶች ኢንዱስትሪ	10,000	20,000	13,260	79,560,000	132,600,000
9.7	የክብሪትና የሰንደል ማምረቻ ኢንዱስትሪ	500	1,000	26,000	19,500,000	39,000,000
9.8	የኦክሲጂን ፣ የሃይድሮጅን እና ሌሎች ጋዞች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	1,000	2,500	23,400	29,250,000	58,500,000
10	የመድሃኒት ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
10.1	የመድሃኒት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	13,000	130,000,000	260,000,000
10.2	የኢታኖል ማረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	20,000	9,750	48,750,000	195,000,000
11	የጎማና የፕላስቲክ ዉጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
11.1	የመኪና ጎማ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	17,680	130,000,000	176,800,000

12	የብረ[illegible] ማዕድን ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ					
12.1	የመስታወትና የመስታወት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	14,950	199,342,000	299,000,000
12.2	የቡሉኬት ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	3,000	5,000	15,600	36,000,000	60,000,000
12.3	የሴራሚክስ ውጤቶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	13,650	182,000,000	273,000,000
12.4	የብረት ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	13,000	173,342,000	260,000,000
12.5	የማርብል፣የግራናይት፣ የላይምስቶን ዲንጋይ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	15,000	20,000	16,250	216,671,000	325,000,000
13	የብረት ውጤቶች ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ					
13.1	የሚስማር፣የቆርቆሮ፣የአጥር ሽቦ እና የመሳሰሉ ዕቃዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	25,000	23,400	[illegible]00,000	117,000,000
13.2	የግብርና ማሽኖች (ኮምባይነር፣ትራክተር …) ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	30,000	26,000	260,000,000	780,000,000
13.3	አነስተኛ የእርሻ መሳሪያዎች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	7,000	19,500	65,000,000	97,500,000
13.4	የመኪና ማምረቻ ኢንዱስትሪ	20,000	30,000	20,800	780,000,000	1,040,000,000

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል
13.5	የሳይክልና የሞተር ሳይክል ማምረቻ ኢንዱስትሪ	7,000	10,000	11,700	78,000,000	117,000,000
13.6	የኤስታቢላይዘር፣ የኤሌቬተር፣ የቦይለር፣ የትራንስፎርመር ፣ የጀኔሬተርና UPS ማምረቻ ኢንዱስትሪ	10,000	15,000	26,000	195,000,000	390,000,000
13.7	የላብራቶሪና የሃኪም ቤት ቁሳቁሶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	70,000	10,000	23,400	78,000,000	117,000,000
13.8	የኮሚኒኬሽን፣የመብራት ገመድና ቁሳቁሶች ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5,000	7,000	1,734	78,000,000	13,006,500
13.9	የጣሳ፣ የቆርኪ፣ ውሃ ማሸጊያ ፕላስቲክ ጠርሙስ እና ክዳን እና የመሳሰሉትን ማምረቻ ኢንዱስትሪ	7,000	10,000	13,260	44,200,000	66,300,000

2. የአገልግሎት ዘርፍ መስፈርት/ስታንዳርድ

ሀ. ግዙፍ ሪል ስቴት እና የነዳጅ ሞቴል ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት፣

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ዓይነት	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)
1	ግዙፍ ሪል ስቴት	60,000	120,000	17,333	800,000,000	1,600,000,000
2	ሞቴል	2,500	3,500	65,000	125,000,000	175,000,000

ለ. የትምህርት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት፣

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
1	አፀደ ሕጻናት					
1.1	መዋዕለ ሕጻናትና ነርሰሪ	4,000	7,000	5,733	17,640,000	30,870,000
2	የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት					
2.1	አንደኛ ደረጃ (1-6)	10,000	15,000	4,940	38,000,000	57,000,000
2.2	መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ (7-8)	10,000	20,000	7,540	58,000,000	116,000,000
2.3	አንደኛና መለስተኛ 2ኛ ደረጃ (1-8)	15,000	20,000	7,540	87,000,000	116,000,000
3	ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት					
3.1	ሁለተኛ ደረጃ (9-12)	[illegible]	60,000	7,670	177,000,000	354,000,000
4	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጅ	25,000	60,000	8,450	195,000,000	390,000,000

ሐ.የጤና ተቋም ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት፣

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ዓይነት	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ሊሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)
1	የመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታል	5,000	10,000	27,300	105,000,000	210,000,000
2	ጠቅላላ ሆስፒታል	10,000	18,000	18,056	138,890,000	250,000,000
3	ኮምፕ/ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	30,000	50,000	15,167	350,010,000	583,350,000
4	ስፔሻላይዝ የህክምና ማዕከላት (የዐይን፣ የጥርስ፣ የህፃናት የመሳሰሉት)	2,000	5,000	32,500	50,000,000	125,000,000

መ.የሆቴል ኢንቨስትመንት በሁሉም የከተሞች ፈርጅና የቦታ ደረጃ (ባለኮከብ ሆቴል)

ተ.ቁ	የፕሮጀክቱ ዓይነት	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)
	ባለ ኮከብ ሆቴል					
1	ባለ አንድ ኮከብ ኢንተርናሽናል ሆቴል	[illegible]00	3,000	81,250	50,000,000	187,500,000
2	ባለ ሁለት ኮከብ ኢንተርናሽናል ሆቴል	1,000	4,000	91,000	70,000,000	280,000,000
3	ባለ ሶስት ኮከብ ኢንተርናሽናል ሆቴል	1,200	5,000	97,500	90,000,000	375,000,000
4	ባለ አራት ኮከብ ኢንተርናሽናል ሆቴል	1,500	6,000	95,333	110,000,000	440,000,000
5	ባለ አምስት ኮከብ ኢንተርናሽናል ሆቴል	2,000	8,000	91,000	140,000,000	560,000,000

	ባለ ኮከብ ሪዞርት	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
1	ባለ አንድ ኮከብ ሪዞርት	6,000	8,000	19,500	90,000,000	120,000,000
2	ባለ ሁለት ኮከብ ሪዞርት	7,000	10,000	20,428	110,000,000	157,142,857
3	ባለ ሦስት ኮከብ ሪዞርት	8,000	12,000	22,750	140,000,000	210,000,000
4	ባለ አራት ኮከብ ሪዞርት	10,000	13,000	20,800	160,000,000	240,000,000
5	ባለ አምስት ኮከብ ሪዞርት	12,000	20,000	19,500	180,000,000	300,000,000
	ሎጅ					
1	ሎጅ	10,000	30,000	16,250	125,000,000	[illegible]

ረ. የገበያ ማዕከል፣ ሞል፣ ሁለገብ ህንፃ እና የፋይናንስ ተቋማትና መሰል አገልግሎቶች (ለሪጂዮ ፖሊስና ፈርጅ አንድ ከተሞች)

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/1ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የማንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ዝቅተኛ ቋሚ የስራ ዕድል	ዝቅተኛ ጊዜያዊ የስራ ዕድል
ሞል	G+4	3,000	3,750	42,841	128,523,000	160,653,750		
	G+5	3,600	3,750	51,409	185,072,400	192,783,750		

	G+6	3,750	4,200	61,691	231,341,250	259,102,200		
	G+7	3,750	4,800	74,029	277,608,750	355,339,200		
	G+8	3,750	5,400	88,835	333,131,250	479,709,000		
	G+9	3,750	6,000	106,602	399,757,500	639,612,000		
	G+10	3,750	6,600	127,922	479,707,500	844,285,200		

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/2ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ዝቅተኛ ቋሚ የስራ ዕድል	ዝቅተኛ ጊዜያዊ የስራ ዕድል
የገበያ ማዕከል፣ሁለገብ ህንጻ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+4	3,750	5,000	32,130	120,487,500	160,653,750		
	G+5	4,000	5,000	38,556	154,224,000	192,783,750		
	G+6	5,000	5,250	49,352	246,760,000	259,102,200		
	G+7	5,000	6,000	59,223	296,115,000	355,339,200		
	G+8	5,000	6,750	71,068	355,340,000	479,709,000		
	G+9	5,000	7,500	85,281	426,405,000	639,612,000		
	G+10	5,000	8,200	102,961	514,805,000	844,285,200		

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/3ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ዝቅተኛ ቋሚ የስራ ዕድል	ዝቅተኛ ጊዜያዊ የስራ ዕድል
የገበያ ማዕከል፣ሁለገብ ህንጻ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+4	5,000	6,000	26,775	133,875,000	160,653,750		
	G+5	6,000	-	32,130	-	192,783,750		
	G+6	6,000	7,000	37,014.6	222,087,600	259,102,200		
	G+7	6,000	8,000	44,417	266,502,000	355,339,200		
	G+8	6,000	9,000	53,301	319,806,000	479,709,000		
	G+9	6,000	10,000	63,961	383,766,000	639,612,000		
	G+10	6,000	11,000	76,753	460,518,000	844,285,200		

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/4ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ዝቅተኛ ቋሚ የስራ ዕድል	ዝቅተኛ ጊዜያዊ የስራ ዕድል
የገበያ ማዕከል፡ሁለገብ ህንጻ፡ ፋይናንስ ተቋማት	G+4	7,500		21,420	-	160,653,750		
	G+5	7,500	9,000	31,420	160,650,000	192,783,750		
	G+6	7,500	10,500	24,676	185,070,000	259,102,200		
	G+7	7,500	12,000	29,611	222,082,500	355,339,200		
	G+8	7,500	13,500	35,534	266,505,000	479,709,000		
	G+9	7,500	15,500	41,265	309,487,500	639,612,000		
	G+10	7,500	16,500	51,168	383,760,000	844,285,200		

➢ ገበያ ማዕከል፣ሞል፣ሁለገብ ህንፃ እና የፋይናንስ ተቋማትና መሰል አገልግሎቶች (ፈርጅ ሁለትና ሦስት ከተሞች)

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/1ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካ/ሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
የገበያ ማዕከል፡ሁለገብ ህንጻ፡ ፋይናንስ ተቋማት	G+3	3,000	5,000	24,716	74,148,000	123,581,250
	G+4	3,750	5,000	32,130	120,487,500	160,653,750
	G+5	4,000	5,000	38,556	154,224,000	192,783,750
	G+6	5,000	5,250	49,352	246,760,000	259,102,200
	G+7	5,000	6,000	59,223	296,115,000	355,339,200
	G+8	5,000	6,750	71,068	355,340,000	479,709,000

	G+9	5,000	7,500	85,281	426,405,000	639,612,000
	G+10	5,000	8,200	102,961	514,805,000	844,285,200

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/2ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
የገበያ ማዕከል፣ ሁለገብ ህንጻ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+3	4,000	6,000	20,596	82,384,000	123,581,250
	G+4	5,000	6,000	26,775	133,875,000	160,653,750
	G+5	6,000	6,500	32,130	192,783,750,	208,845,000
	G+6	6,000	7,000	37,014	222,084,000	259,102,200
	G+7	6,000	8,000	44,417	266,502,000	355,339,200
	G+8	6,000	9,000	53,301	319,806,000	479,709,000
	G+9	6,000	10,000	63,961	383,766,000	639,612,000
	G+10	6,000	11,000	76,753	460,518,000	844,285,200

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/3ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠቅላላ ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
የገበያ ማዕከል፣ሁለገብ ህንጻ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+3	6,000	7,500	16,477	98,862,000	123,581,250
	G+4	7,500	8,000	21,420	139,300,000	171,300,000
	G+5	7,500	9,000	21,420	160,650,000	192,783,750
	G+6	7,500	10,500	24,676	185,070,000	259,102,200
	G+7	7,500	12,000	29,611	222,082,500	355,339,200
	G+8	7,500	13,500	35,534	266,505,000	479,709,000
	G+9	7,500	15,500	41,265	309,487,500	639,612,000

	G+10	7,500	16,500	51,168	383,760,000	844,285,200

❖ ፈርጅ አራትና አምስት ከተሞች

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/1ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሬ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሬ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሬ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
የገበያ ማዕከል፣ሁለገብ ህንጻ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+2	3,000	6,000	15,843	47,529,000	95,062,500
	G+3	4,000	6,000	20,596	82,384,000	123,581,250
	G+4	5,000	6,000	26,775	133,875,000	160,653,750
	G+5	6,000	6,500	32,130	192,783,750	208,845,500
	G+6	6,000	7,000	37,014	222,084,000	259,102,200
	G+7	6,000	8,000	44,417	266,502,000	355,339,200
	G+8	6,000	9,000	53,301	319,806,000	479,709,000
	G+9	6,000	10,000	63,961	383,766,000	639,612,000
	G+10	6,000	11,000	76,753	460,518,000	844,285,200

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/2ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የግንባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሬ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሬ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካሬ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
የገበያ ማዕከል፣ሁለገብ ህንጻ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+2	4,500	7,500	12,675	57,037,500	95,062,500
	G+3	6,000	7,500	16,477	98,862,000	123,581,250
	G+4	7,500	8,000	21,420	159,300,000	171,300,000
	G+5	7,500	9,000	21,420	160,650,000	192,783,750
	G+6	7,500	10,500	24,676	185,070,000	259,102,200
	G+7	7,500	12,000	29,611	222,082,500	355,339,200
	G+8	7,500	13,500	35,534	266,505,000	479,709,000
	G+9	7,500	15,500	41,265	309,487,500	639,612,000

	G+10	7,500	16,500	51,168	383,760,000	844,285,200

- በከተማ ውስጥ በደረጃ (1/3ኛ) ተግባራዊ የሚደረግ

የፕሮጀክቱ ዓይነት	የማገባታው ከፍታ	ዝቅተኛ የመሬት መጠን በካሜ	ከፍተኛ የመሬት መጠን በካሜ	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመን ካፒታል (በብር)
የግል ማስለሁለገብ ሀንፃ፣ ፋይናንስ ተቋማት	G+2	9,000	10,000	9,506	85,554,000	95,062,500
	G+3	10,000	12,000	10,298	102,980,000	123,581,250
	G+4	10,000	15,000	10,710	107,100,000	160,653,750
	G+5	10,000	18,000	10,710	107,100,000	192,783,750
	G+6	10,000	21,000	12,338	123,380,000	259,102,200
	G+7	10,000	24,000	14,805	148,050,000	355,339,200
	G+8	10,000	27,000	17,767	177,670,000	479,709,000
	G+9	10,000	30,000	21,320	213,200,000	639,612,000
	G+10	10,000	33,000	25,384	255,840,000	844,285,200

3. የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት መስፈርት/ስታንዳርድ፣

1. በገጠር ኢንቨስትመንት መሬት የሚተገበር የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ስታንዳርድ፣

ሀ. እርሻ ኢንቨስትመንት

ቁጥር	የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አይነት	የሚለማበት ሁኔታ	አንድ ሄክታር ለማልማት የሚያስፈልግ ካፒታል በአማካይ (ብር/ሄ/ር)	ምርመራ
1	የእርሻ ልማት			
1.1	የዓመታዊ ሰብሎች ልማት፣			
1.1.1	የብርዕ፣ የአገዳ፣ የጥራጥሬ፣የቅባት እና ሌሎች ሰብሎች ልማት	በመስኖ	138,000	
1.1.2	የተረጋገጠ ምርጥ ዘር ማምረት			
1.1..2.1	የዓመታዊ ሰብል ምርጥ ዘር	በመስኖ	182,989	
1.1..2..2	የአትክልት ምርጥ ዘር	በመስኖ	182,989	
1.1.3	እፀ ጣዕም ልማት፣			
1.1.3.1	ዕፀ-ጣዕም በገሪን ሀውስ	በመስኖ	9,562,696	
1.1.3.2	ዕፀ-ጣዕም ከገሪን ሀውስ ውጭ	በመስኖ	5,954,952	
1.1.4	አትክልት ልማት			
1.1.5	አትክልት ልማት	በመስኖ	284,496	
1.1.6	የሥራስር ሰብሎች ልማት (ድንች፣ ስኳር ድንች፣ካሳቫ የመሳሰሉት)	በመስኖ	144,918	
1.1.7	የእንስሳት መኖ ማምረት	በመስኖ	265,586	
1.2	የመካከለኛ ጊዜ ቋሚ ተክሎች ልማት			
1.2.1	አበባ ልማት			
1.2..2	አበባ ልማት በገሪን ሀውስ	በመስኖ	11,953,370	
1.2..3	አበባ ልማት ከገሪን ሀውስ ውጭ	በመስኖ	7,443,690	
1.2.2	ቅመማ ቅመም ልማት	በመስኖ	472,094	

ቁጥር	የግብርና ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አይነት	የሚለማበት ሁኔታ	አንድ ሄክታር ለማልማት የሚያስፈልግ ካፒታል በአማካይ (ብር/ሄ/ር)	ምርመራ
1.3	የቋሚ ተክሎች ልማት			
1.3.1	የረዥም ጊዜ ፍራፍሬዎች ልማት(ብርቱኳን፣ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ መንደሪን፣ አፕል የመሳሰሉት)	በመስኖ	371,800	በዝናብና ተጨማሪ መስኖ
1.3.2	ፓፓያ ልማት፣	በመስኖ	329,550	
1.3.3	ሙዝ ልማት፣	በመስኖ	414,657	
1.3.4	የእንቴ ተክሎች ልማት			
	ቡና ልማት	በዝናብ	455,399	በዝናብና ተጨማሪ መስኖ
	ሻይ ልማት	በዝናብ	538,545	
1.4	የኢንዱስትሪ ተክሎች ልማት			
1.4.1	ሞሪንጋ	በዝናብ	253,500	
1.4.2	ጥጥ	በመስኖ	149,396	በዝናብና ተጨማሪ መስኖ
1.4.3	ሸንኮራ አገዳ	በመስኖ	261,452	
1.4.4	የጎማ ዛፍ	በዝናብ	205,245	
1.4.5	ታንጫ	በዝናብ	143,650	
1.4.6	የነዳጅ እፅዋት ምርት/ጃትሮፋ/ጉሎ የመሳሰሉት	በዝናብ	143,650	
1.5	የደን ልማት	በዝናብ	143,650	

ለ. የእንስሳት ዘርፍ ኢንቨስትመንት

1. በገጠር የሚተገበር እንስሳት ዘርፍ ኢንቨስትመንት

ተ.ቁ	የማብርና እንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አይነት	ዝቅተኛ የእንስሳት ቁጥር	ለማልማት የሚያስፈልግ አማካይ ካፒታል (ብር/ሄ/ር)	ዝቅተኛ የመሬት መጠን	ዝቅተኛ ኢንቨስትመንት ካፒታል በብር	መርመራ
2	የእንስሳት ሀብት ልማት					
2.1	የቤት እንስሳት ልማት					
2.1.1	የወተት ከብት እርባታ	50	10,400,000	3 ሄ/ር	62,400,000	
2.1.2	የበግ/ፍየል እርባታ	500	7,800,000	3ሄ/ር	46,800,000	
2.1.3	ከብት ማድለብ	300	13,873,600	3 ሄ/ር	83,241,600	
2.1.4	በግና ፍየል ማድለብ ስራ	1,000	13,000,000	3ሄ/ር	45,500,000	
2.1.5	የዶሮ እርባታ	20,000	23,658,827	2 ሄ/ር	106,586,222	
2.2	የዱር እንስሳት ልማት					
2.2.1	የአሳማ እርባታ	500	13,000,000	4 ሄ/ር	40,000,000	
2.2.2	የአዞ እርባታ	350	21,552,960	1.5ሄ/ር	24,868,800	በሰው ሰራሽ ኩሬ ማርባት (ቢያንስ
2.2.3	የዓሳ እርባታ	10,000	19,593,600	5 ሄ/ር	75,360,000	በሰው ሰራሽ ኩሬ ማርባት (ቢያንስ
2.2.4	ንብ ማነብ/ማር ማምረት	1,000ቀፎ	9,100,000	5 ሄ/ር	35,000,000	1000 ዘመናዊ ቀፎ
2.2.5	የሀር ትል ልማት	-	5,200,000	10 ሄ/ር	40,000,000	በዘናብና ተጨማሪ መስኖ

II. በከተማ የሚተገበር የእንስሳት ዘርፍ ኢንቨስትመንት

ተ.ቁ	መግለጫ	ዝቅተኛ የእንስሳት ቁጥር	ዝቅተኛ የመሬት መጠን (በካ/ሜ)	ከፍተኛ የመሬት መጠን (በካ/ሜ)	አማካይ ካፒታል በካሬ ሜትር (ብር/ካ/ሜ)	ለዝቅተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ለኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)	ለከፍተኛ የመሬት መጠን የሚያስፈልግ ጠ/ኢንቨስትመንት ካፒታል (በብር)
1	የወተት ከብት እርባታ	25	5,000	10,000	13,000	50,000,000	100,000,000
2	የዶሮ እርባታ	10,000	1,000	5,000	26,000	20,000,000	100,000,000
3	አትክልትና ፍራፍሬ ልማት	-	50,000	100,000	520	20,000,000	40,00,0000
4	የእበባ ምርት በግሪን ሀውስ ውስጥ	-	100,000	200,000	919	70,730,000	141,460,000
5	የእበባ ምርት በሜዳ ላይ	-	50,000	200,000	573	22,025,000	88,100,000
6	ዕፀ-ጣዕም ልማት በግሪን ሀውስ		100,000	200,000	736	56,580,000	113,160,000
7	ዕፀ-ጣዕም ከግሪን ሀውስ ውጪ		100,000	200,000	455	35,000,000	70,000,000